# ልማታዊ ፓትርያርክ

ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ

nigatuasteraye@gmail.com

ግንቦት ፳፻፮ ዓ.ም.

## መግቢያ

ይህችን ክታብ በዚህ ርእስ እንዳዘጋጅ ያነሳሳችኝ “ልማታዊ መንግስት-እንደ ቻይና፤ ነገሩስ ባልከፋ” በሚል ርእስ ዶ/ር ደስታው አንዳርጌ ግንቦት ፲ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም ያቀረቡልን ክታብ ናት። [ሙሉውን እዚህ ላይ በመጫን ያንብቡ። ] ከሀ እስከ ሠ ተዘርዝራ የቀረበችውን ይህችን ክታብ ሳነብ፤ እንደኔ ያለውን እንቅልፋም ተማሪ ቀስቃሽ ምሁር፤ በክታባቸው አማካይነት ጣቴን ይዘው ወደ ጠቀሷቸው አገሮች ወደ እስያ፤ ቻይና፤ ታይዋንና ጃፓን በመንፈስ ወሰዱኝ።

ተመልከት! ልማታዊ መንግስት ይሉሀል። ሰላም በምድራቸው፤ በጎ ፈቃድ በዜጎቻቸው አዕምሮ እና ስነ ልቡና ላይ ልማትን የመሰረቱ እነዚህ የቻይና የጃፓንና የታይዋን መንግስታት ናቸው። የኢትዮጵያ መንግሥት የዘረጋው የልማት ግን፤ በጅብና በአህያ፤ በተኩላና በበግ፤ በጃርትና በዱባ መካከል የተዘረጋ የልማታ ተቃራኒ ጥፋት ነው።” እያሉ በማነጻጸር ያስጎበኙኝ መሰለኝ።

ቀጥለውም፤ “የኢትዮጵያን ግማሽ ህዝብ ያቀፈችውን ኢትዮጵያዊቷን ቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያንን እመራለሁ ብለው ፓትርያርክ ነኝ የሚሉት “ካዲስ አበባ ወጥቼ በየገጠሩ ስዘዋወር ዓለም ያደነቀው ልማት ሲጣደፍ አየሁ” እያሉ ሲናገሩ ሰምተሀል። አንተ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በዘረጉት ያብነት ጉባዔ ተሳትፌያለሁ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ትክክለኛ ቄስ ነኝ የምትል ከሆነ፤ ያስጎበኘሁህን አይተህ፤ የነገርኩህን ሰምተህና ተረድተህ፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መምህራን ካስተማሩህ የልማት ዘይቤ ጋራ አነጻጽረህ በክህነታዊ ሀለፊነትህ የምትለው ለማለት አትፍራ” ያሉኝም መሰለኝ።

በዚህ ስሜት ላይ ሆኘ ክታቧን ለመጨረስ ቀጥየ ሳነብ፤ በተራ ዝርዝር ሐ ላይ “የአገር ፍቅርና የሃላፊነት ስሜት” በምትለው አንቀጽ ስር፤ እኛ ኢትዮጵያውያን የተሰለፍንበት መስክ የሚጠይቀንን ሀላፊነት መውሰድ የማንችል ደካሞች መሆናችንን ለማሳየት እኚሁ የተከበሩ መምህራችን ብዙ ምሳሌዎችን ከጠቀሱ በኋል “ለበጎውም ለክፉውም ተጠያቂው ሁልጊዜ ሌላ ነው። . . . . . . . ራስን መጠየቅ፤ እውነትን መጋፈጥ መንፈሳዊ ወኔ ይጠይቃላ።” ካሏት እንደ ጦር ፍላጽ ከምትናደፈው ቃለ አጋኖ ላይ ደረስኩ።

በጥልቅ ትዝብት ውስጥ የሰመጡ እኚህ መምህር እየደጋገሙ “አንተም የዚህች ቤተ ክርስቲያን ቄስ ነኝ የምትል ከሆነ ከመንፈሳዊ ሀላፊነት አትሸሽ! የወያኔ ፓትርያርክ አባ ማትያስ፤ ኢህደግ በኢትዮጵያ የዘረጋውን የጥፋት መረብ ደብቀው፤ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት በጥርጥር የሚመለከቱትን በዓለም ትዝብታ ላይ የወደቀውን የወያኔውን ልማት “ዓለም ያደነቀው” በማለት፤ የዘንድሮውን ርክበ ካህናት የከፈቱበትን ከመስመር የወጣውን ንግግር በጥሞና አዳምጥ።

የሳቸውን ንግግር በሰጠሁህ ቅርጽና ይዘት ለክተህ፤ እያስተማሩ ባሳደጉህ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ልማታዊ መስፈርት ሰፍረህ “ልማታዊ ፓትርያርክ” በሚል ርእስ አቅርብ፤ ብለው ያዘዙኝ ስለመሰለኝ። ከዚህ በታች በተዘረዘሩት

- ልማታዊ ፓትርያርክ ዝክረ ነገሩ የጠራ (የተቀደሰ) ሊሆን ይገባል።
- ደገኛና የተቀደሰ ምክር የሚፈልቀው ዝክረ ነገሩ ከጠራ ፓትርያርክ ነው።
- የክርስቶሳዊና የሐዋርያዊ ሲኖዶስ የመነጋገሪያ ዓበይት ነገሮች

“ልማታዊ ፓትርያርክ” በሚል ርእስ ከዚህ በላይ በገለጽኳቸው ሶስት አንቀጾች፤ ይህችን የቤት ስራ ለኢትዮጵጵያውያን ወገኖቼ ለማቅረብ ተገደድኩ።

# ክፍል አንድ:- ፓትርያርክ

## ፩ኛ:-የፓትርያርክ ዝክረ-ነገር እና ምክር

የፓትርያርክ ዝክረ-ነገር እና ምክር ምን መምሰል እንዳለባቸው እነመልከታቸው፡፡

ሀ. የፓትርያርክ ዝክረ ነገር

ለ.የፓትርያርክ ሠናይት ምክር

### ሀ. የፓትርያርክ ዝክረ ነገር:-

በሊቃውንት (በነገረ መለኮት፤ በህክምና፤ በምህንድስና በህግ ና በሌሎችም የምንኖርባትን ምድር መተርጎም በሚስችሉ ዘርፎች በበሰሉ ክርስቲያኖች) ሲመዘን የጠራ ሊሆን ይገባል፡፡

ፓትርያርካዊ ዝክረ ነገር ስል; ስለተለመደው ለጻድቃን መታሰቢያ ስለሚዘጋጀው ጠበል ጻሪቅ ማለቴ አለመሆኑን ማስገንዘብ አወዳለሁ፡፡ ለጻድቃን መታሰቢያ የሚዘጋጀው ጠበል ጻሪቅ፤ ቅዱሱ በህይወቱ ሳለ መስዋዕት ለከፈለለት ዝክረ ነገር ዘርፍ ወይም እንፍርፋሪ እንጅ ዝክር አይደለም፡፡ ለአጽንኦ እደግመዋለሁ፡፡ ዝክር ማለት፤ ሰው ከፉም ይሁን መልካም በመስራት በማህበረ ሰቡ አዕምሮ ላይ የሚቀርጸው፡ ከመቃብር በላይ የሚኖር የታሪኩ ትዝታ ነው፡፡

“ከእንጨት የንቅዘት ባህርይ የሌለበትን መርጦ ለታቦት፤ ከሰውም የእምነት ሕጸጽ የሞራል እንከን የሌለበትን መርጦ ለሹመት” እንዲሉ፤ ከጠቅላላው ህዝበ ክርስቲያን መካከል መታጨበት ያለበት ፓትርያርክ ሊቀ ህሩያን ማለትም ከተመረጡት ውስጥ ነጥሮ በመውጣት የተመረጠ ማለት ነው፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ “ቅድመ አዕምር ስሞ ለበአለ ዝንቱ” እንዳለው፤ ህዝበ ክርስቲያን የፓትርያርኩን የዝክረ ነገር ጥራት የማረጋገጥ መብት አለው፡፡ መጀመሪያ ወደ መንበሩ ከመምጣቱ በፊት፤ ፓትርያርካዊው ምክሩ ተቀባይነትን ያገኝ ዘንድ ህዝቡ በሚረዳውና በሚገባው ግልጽ በሆነ መንገድ በህዝብ አዕምሮ ላይ ያስቀመጠውን መጥፎ ዝክረ ነገር ካለ፤ ከህዝቡ ጭንቅላት ማጽዳት አለበት፡፡ ህዝቡን ለንስሀ የሚጠራ፤ ህዝባዊ ንስሀ አበት ነውና፡ ለህዝባዊ ኑዛዜ ምሳሌ ይሆን ዘንድ የሰራውን ስህተት እየተናገረ ዝክረ ነገሩን ሳይደብቅ እየተናዘዘ ወደ መንበረ ፓትርያርኩ የመቅረብ ግዴታና ሀላፊነት አለበት፡፡ እራስን የማጋለጥ ሀላፊነትን ያልሸሸ ጀግና (ቅዱስ) መሆን አለበት፡፡ የፓትርያርክ ዝክረ_ነገር (ትዝታ) ያለፉትን ቅዱሳን ሰማእታት ዝክረ ነገር የሚያስታውስ በመሆኑ እንደወርቅ ነጥሮ የጠራ፤ ጽርየቱም እየፈለቀ ከሩቅ የሚስብና የሚጠራ መሆን አለበት፡፡ ካንደበቱ ለሚጎርፈው ምክር እንቅፋት መሰናክልና መዝጊያ የሆነ ነገር በሚመክራቸው ሰዎች ጭንቅላት ፈጽሞ፤ ፈጽሞ፤ ፈጽሞ መኖር የለበትም፡፡

በዚህ አይነት መንገድ ዝክሩን እያጠራ ወደ መንበሩ ከሚመጣ ፓትርያርክ የምትፈልቅ ምክር “ምክር ሠናይት ለኩሉ ዘይገብራ” ትባላላች፡፡ ማለትም ፈጣሪን ከፍጥረቱ፤ ህዝብን ከመንግስቱ፤ በየመንደሩ ሰፍሮ የሚኖረውን ዜጋ ከሠራዊቱ ጋራ የምትስማማ ደገኛ ምክር ብሎ ሰሚ አድማጭ ሁሉ ያላንዳች ጥርጥርና ጥያቄ ይቀበላታል፡፡

### ለ. የፓትርያርክ ሠናይት (ደገኛ) ምክር:-

የፓትርያርክ ምክር፤ ከነገረ ዝክሩ ጋራ መስማማት አለባት፡፡ “ምክር ሠናይት_ለኩሉ ዘይገብራ”፤ ብሎ ዳዊት የተናገረላት ደገኛ ምክር፤ በጥበብና በዘላለማዊነት የታጀበች ናት፡፡ ዳዊት “ምክር ሠናይት_ለኩሉ ዘይገብራ” ከማለቱ በፊት “ቀዳሚሃ ለጥበበ ፈሪሃ እግዚአብሄር” የሚለውን አስቀደመ፡፡ “ምክር ሠናይት ለኩሉ ዘይገብራ” ካለም በኋላ፤ “ወስብሐቲሁኒ ይነብር ለዓለም” በምትለው ሀረግ ዘጋት፡፡

ጌታችን “እስመ ኢከሰተ ለከ ዘሥጋ ወደም አላ አቡየ ዘበሰማያት” ማለትም ሰማያዊ አባቴ እንጅ፡ ሥጋዊ ደማዊ መምህር ያስተማረህ አይደለም፡፡”እንዳለው፤ በዚህ መስመር የሚመክር ሰው ምክሩ ከምድራዊ ገዥ የተሰወረች፤ ከፈሪሃ እግዚአብሄር የመነጨች ህዝብን ከጨለማ የምታወጣ ጥበብ ናት፡፡ ይህች አይነት ምክር “ወስብሐቲሁኒ ይነብር ለዓለም” (መዝ ፻፲፡፰__፱) ከምትለው ድምዳሜ ላይ የምታደርስ ናት፡፡ ማለትም፤ እንደሙሴ “ወይረድ ከመ ጠል ነቢብየ” ለመባል የበቃች፤ ፈጣሪው ያከበረውን ሰው ከዘላለማዊ ክብሩ እንዳይገፈፍ የምታሳስብ በረከትና ሰላም የተሞላች ምክር ትሆናላች፡፡

ምክር ፡ ያለ ሠናይት ዝክር፤ የማታፈራ ያረረች ዘር ናት፡፡ ዝክርም ያለ ደገኛ ምክር፤ በእንቅብ የተሸፈነች መብራት ናት፡፡ በጠቅላላው፤ ዝክር የመካሪው መሰረታዊውና መታሰቢያው መታወቂያው ናትና ዝክሩ የተበላሸ ከሆነ ከተበላሸ ዝክር የሚፈልቅ ምክር የህዝብን ማስተዋል የሚጋርድ አዚም ነው፡፡

ምክሩና ዝክሩ የተሰማማለት ፓትርያርክ ከፈጣሪ በታች ህዝባዊ "ርእሰ አምሮ" ማለትም፤ እንደ አቡነ ጴጥሮስ ለእምነት ለታሪክ ተላልፎ ሊሰዋ የተዘጋጀ፤ ለእምነት ለታሪክ ለህዝብ ተጋርደው ለመሞት ለሚዘጋጁ ሁሉ ምሳሌ የሆነ አባት ማለት ነው። ፊላታዎስ የተባለው ሊቅ "ሰበክነ ስመከ ልዕልተ ወክብርተ ውስተ ኩሎን አብያተ ክርስቲያናት ወውስተ ኩሎን አህጉር ወበህውርት ወአዘዝነ ይዝክሩከ በኩሉ ቅዳሴያት ወእግዚ ልዑል ያጽንዕ ስመከ ወስብሀት ለአምላክነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላመ ለኩሎሙ እለ ሀለው ታሕተ ሥልጣንከ ወእለ ይገርሩ ለመንበርከ" (ሃይ ፸፭፡ ፲፫) ብሎ የተናገረለትን ደገኛና ታማኝ ፓትርያርክ የሚመስለ ማለት ነው። ፊላታዎስ ስለ ታማኙ ፓትርያርክ "ካህናት ሊቃውንት ህዝበ ክርስቲያን በዝክር ሠናይ ስለ አጌጠች ስምህ ዝናህ በየ አገሩ በየደብሩ በየገዳማቱ ላሉት ለካህናት ለሊቃውንት ለመነኮሳት ለህዝበ ክርስቲያን ነገርን። ስምህም በቅዳሴያችን እንዲታወስ አደረግን። ምስክርነትህን እግዚአብሔር ይባርክልህ። ይህን ላደረገ ጌታ ክብር ምስጋና ይገባዋል። ባንተ አመራር ጥላ ስር ላሉት ሁሉ ሰላም እንዳይጎድልባቸው እንጸልያለን።" ይሉታል።

የፓትርያርክ ዝክረ ነገር ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ሊቁ የገለጸበት አረፍተ ነገር፤ ጌታችን ሲወለድ በእረኞች መካከል በምድር ከነበረው መላክ ጋራ የነበሩት የሰማይ ሠራዊት "ስብሀት ለእግዚ በሰማያት ወሰላም በምድር ስምረቱ ለሰብእ" ብለው የተናገሩትን ለየት ባለ አነጋገር በማቅረብ ነው።

ፓትርያርክ ለህዝብ የሚያቀርበው ምክር እውቀት ጥበብ ርህራሄ ሰላም ተግሳጽ ከፈጣሪ ብቻ የሚቀበለው መሆን አለበት። ከፈጣሪ የሚቀበለው ከሆነ የሚመራትን ቤተ ክርስቲያን ለይቶ የሚያውቅ በሰማይ ያለ አምላክን የሚያስከብር በምድር ላይም በሰው ልብ ሰላም እንዲሰፍን በጎ ፈቃድ እንዲሰርጽ ማድረግ ይችላል። ለሰው ልዕልና። ክብር ጥብቅና የሚቆም፤ ለምድራዊ ኃይል ታዛዥ ያልሆነ፤ በምድራዊ ሃይል ታዝሎና ሰላምን ጥሶ በጎ ፈቃድን ገሶ ወደ መንበረ ፓትርያርክ ያልገባ ማለት ነው። ዝክረ ነገሩ ከጠራ ፓትርያርክ የምትፈልቀው ልማታዊት (ደገኛ) ምክር ከዚህ በታች እንመልከት።

# <u>፪ኛ፡- ዝክሩና ምክሩ ከተጣጣሙለት ልማታዊ ፓትርያርክ የሚፈልቁ የተቀደሱ ምክርና ትምህርት</u>፡-

ዝክሩና ምክሩ ከተጣጣሙለት ፓትርያርክ የሚፈልቁ ምክርና ትምህርት፤ በጥንተ ተፈጥሮ ፈጣሪ ለሰው ከሰጣቸው ከሀ እስከ መ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት አበይት መመሪያዎች የሚፈልቁ ናቸው።

**ሀ፡-** "ንግበር ሰብአ በአርያነ ወበአምሳሊነ። ከመ ይኮንን አሳተ ባህር ወአዕዋፈ ሰማይ ወአራዊተ ምድር ወእንስሳሂ ወኩሎ ምድረ ወዘኩሎ ይትሀወስ ዲበ ምድር (ዘፍ ፩፡፳፮)"። ይህ ቃል የሚያሰየው ሰው በፈጣሪው አርያ የተፈጠረ ስለሆነ፤ ፍጡር እንጅ ፈጣሪ ባለመሆኑ፤ እንደ አርያው ፈጣሪ ባይመለከም፤ እንደ ፈጣሪው አርያው ግን መከበር አለበት። የተፈጠረውም ተገዥ ለመሆን ሳይሆን በምድር ያለውን እንዲገዛ ነው። ፓትርያርክ በኃይል የመግዛትንና የመገዛትን መንፈስ መቀበል እንደሌለበት መናገር መምከር አለበት። ይህን የማይናገር የሚደብቅ ፓትርያርክ ተቀባይነት የለውም።

**ለ፡-**ብዝሁ ወተባዝሁ ወምልዕዋ ለምድር ወቅንይዋ ወኮንንዋ" (ዘፍ ፩፡ ፳፰)። ማለትም፡- <u>ልዩ ተአምር ሊገልጽባቸው ከተጠሩ እንደ እነ እንጦንስ ከመሰሉ ልዩ ሰዎች በቀር፤ እግዚአብሄር አንድ ወንድ አንድ ሴት አድርጎ ፈጠረ እንጅ፤ አዳምንና ሄዋንን አመንኩሶ አልፈጠራቸውም።</u> ፈጣሪ ፍጥረቱን ባንድ ወንድና ባንድ ሴት መካከል በሚፈጸም ቅዱስ ሩካቤ እየተባዛ ምድርን ይሞላ ዘንድ፤ ወንድና ሴት አድርጎ ከፈጠረ በኋላ ምድርን እየሞላ እንዲያለማት ፍጥረቱን አዘዘ። ሰው እየተባዛ ምድርን እንዲሞላትና እንዲያለማት የታዘዘ መሆኑንና መባዛትና ማልማት የማይሻሩ ዶክትሪን መሆናቸውን ፓትርያርክ አጠንክሮ መስበክ አለበት። <u>ለዚህ ምሳሌ ብቁአን ያልሆኑት መስለው የገቡትን ካህናት መነኮሳትና ጳጳሳትን በግልጽ እያወገዘ የማይናገር ፓትርያርክ ተቀባይነት የለውም።</u>

**ሐ፡-** "ወሀብኩክሙ ኩሎ ሐመልማለ ሳእር ዘይዘራእ ወይበቁል በበዘርኡ ወትዘርእዎ ዲበ ኩሉ ምድር ወኩሎ እጸ ዘሀሎ ውስቴቱ ዘርኡ ዘይዘራእ በበፍሬሁ ለከሙ ይኩንክሙ ሙብልዓ"(ዘፍ ፩፡ ፳፱)። ይህም ማለት፤ ፈጣሪ ሰውን ከፈጠረ በኋላ አካባቢውን እንዲቆጣጠርና እንዲያለማ እውቀትና ስልጣን አስታጠቀው። በዚህ ስርአት ለሚኖረው ቅዱስ ህዝብ እየተባዛ ምድርን በመሙላት እና በምድር ላይ ያሉትን እንዲገዛና እንዲያለማ የማይገሰስ ቅዱስና ሙሉ ስልጣን ሰጠው። ይህን በግልጽ በድፍረት የማይናገር ፓትርያርክ ተቀባይነት የለውም።

**መ፡-** "ወነሥአ እግዚአብሔር ለእጓለ እመሀያው ዘገብሮ ውሤሞ ውስተ ገነት ከመ ይትገበራ ወይዕቀባ (ዘፍ ፩፡፲፩) የሚለውና "በሀፈ ገጽከ ብላዕ ህብስተከ እስከ ትገብእ ውስተ መሬት እንተ እምኔሃ መጻከ" (ዘፍ ፫፡፲፱)። እነዚህ ሐረጎች ከቦታ በቀር አንድ ናቸው። ሁለቱም የሚያሳዩት በገነትም ሆነ በምድር ፈጣሪ ለፈጠረው ለሰው የማልማትና የመጠበቅ የሰጠው ስልጣንና ሙብት ነው። ሰው በገነታዊ ህይወቱ የተሰጠው የማበጀት እና የመንከባከብ ስልጣኑ ሳይገሰስ፤ ከገነት ከወጥቶ ወደ ምድር ከተመለሰ በኋላም፤ ወደ መጣባት ምድር በሞት እስኪመለስ ድረስ በምድራዊ ህይወቱ፤ የመንከባከቡና የመጠበቁ ሃላፊነት ከጣርና ከጋር ጋራ ተደምሮ፤ ያለ አፈናቃይና ወራሪ የራሱን ምድር በራሱ ወዝ እያለማ እንዲኖር ታዘዘ። ተፈናቃዮችና ተወራሪዎች በሚገኙበት አገር የሚኖር ፓትርያርክ፤ መፈናቀልና ማፈናቀል; መውረርና መወረር እንዳይኖር የሚያሳየውን መለኮታዊ ህግና ትእዛዝ በድፍረትና በግልጽ የማይናገር ከሆነ ተቀባይነት የለውም።

ፈጣሪ በጥንተ ፍጥረቱ ለፈጠረው ሰው የሰጠውን ሙብት ተረድቶ በሚመሰክር ልማታዊ ፓትርያርክ የሚመራ ክርስቶሳዊ ሐዋርያዊና ልማታዊ ሲኖዶስ (ጉባዔ) የሚነጋገርባቸው ዓበይት ነገሮች የሚከተሉት ናቸው።

# ክፍል ሁለት፡- ሲኖዶስ

## ክርስቶሳዊና ሐዋርያዊ ሲኖዶስ የመነጋገሪያ ዓበይት ነገሮች

ክርስቶሳዊና ሐዋርያዊ ሲኖዶስ ይመሩ የነበሩ ሰዎች ከህዝበ ክርስቲያኑ ፍላጎትና ጥቅም የተለየ ባእድ ነገር ህዝብን ላለማሸከም ያደረጉትን ቅድመ ዝግጅት እንመልከት።

የመጀመሪያውን ሲኖዶስ የመሩት ሐዋርያት መጀመሪያ ከህዝብ ጋራ በመነጋገር የልማት መሰረት የሆኑትን ነገሮች ማመንጨት ይችላሉ ብለው የተገነዘቧቸውን የመንፈስ፤ የሞራል፤ የሰላም ልኡካን አስቀድመው ማዘጋጀት እንዳለባቸው ተገነዘቡ። “ኀቢረነ ኀረይነ ዕደወ ዘንፌኑ ኀቤክሙ ምስለ አኀዊነ በርናባስ ወጳውሎስ ዕለ መጠው ነፍሶሙ በእንተ ስሙ ለክርስቶስ” (፲፭፡ ፳፭) መጀመሪያ የልማት መሰረት የሆነውን እግዚአብሔር ለቅዱሱ ሲኖዶስ ያፈሰሰውን ልማታዊ ምክር፤ እምነት፤ ሞራል፤ ጥበብና እውቀት  ለህዝብ የሚያካፍሉ፤ የህዝቡንም ጠቅላላ ሁኔታ ተመልከተው፤ በህዝቡ ላይ የከበደውን ሸክም ተረድተው ለተቀደሰው ልማታዊ ሲኖዶስ መነጋገሪያ የተቀደሱ ዓበይት ነገሮችን የሚያቀርቡ መንፈስ ልዑላን፤ የሥነ ልቡና ኃያላን፤ ህይወታቸውንም ለጽድቅ አምላክ ክብር መገለጫ አድርገው ያቀረቡትን በርናባስን፤ ጳውሎስን፤ ሲላስንና ይሁዳን ወደ ህዝብ ላኩ።

ከሐዋርያት በኋላም የነበሩ ሊቃውንትም ይህን ምሳሌ በመከተል፤ የተቀደሱ ዓበይት ነገሮችን የሚያቀርቡ መንፈስ ልዑላን። የሥነ ልቡና ኃያላን የሆኑ ሰዎች ወደ ህዝብ ላኩ። “ወሶበ በጽሐ ኀቤነ እሉ እለ ሕኑጻን በጥበብ ወበምግባር ተፈሳህነ ቦሙ ጥቀ ዘከመ ርኢነ ገጸከ ወረከብናሆሙ ዘበአማን ድልዋን ለክህነት ወበእንተ ዘኮኑ ላእካነ ዕርቅ ማእከሌነ ይዕስዮሙ እግዚ ዕሤተ በሠናይ ወከማሁ ለዮሐንስኒ ረድእከ ቀሲስ ጻድቅ ተጋዳሊ ትሩፍ ወለሰሎሞን ዲያቆን ቡሩክ ለእሉ ኩሎሙ ተአማኀናሆሙ በፍስሀ ወበሐሴት ወበጻሕቅ እስመ እሙንቱ ተፈልጡ እምቅድሳቲከ ወመጽኡ ኀቤነ ተአዚዞሙ በጻህቅ ለአብናከ” (ሃይ ፻፬፡፲፪) ተብሎ ከተመዘገበው መረጃ እደምንረዳው፤ “በጥበብ በስነ ምግባር እጅግ አረኩን፤ በነሱ ውስጥ በሚንጸባረቀው ሞራልና ጥበብም በአንተ ውስጥ ያለውን አስረዱን። በእርግጥም ለተቀደሰችው ክህነታዊ አገልግሎት የበቁ ሆነው አገኘናቸው። እግዚአብሔር ዋጋቸውን ይከፈላቸውና፤ የላካቸው ቀሲስ ዮሐንስና ዲያቆን ሰሎሞን ለእርቅና ለሰላም የበቁ፤ ለእውነት የሚሰው፤ ምግባራቸው የሰፋ፤ የተባረኩ ሆነው ተረዳናቸው። እነሱ በተልእኳቸው ከቅድስናህ የመነጨውን ጥበብ ይዘውልን በመድረስ ያባትነትህን ሀላፊነት የተወጡ ናቸው። መርጠህ በላክልን ልዑካን ተልእኮ የረኩ ሁሉ እጅ ይነሳሉ።” እያሉ ህዝቡ ስለተላኩት ልኡካንና ስለላኪው ፓትርያርክ ብቃትና ቅድስና ተናገሩ።

በዚህ መንፈሳዊ ተልእኮ የተሰማሩት ሀዋርያትም ሊቃውንትም፤ ከዚህ በታች ከ፩ እስከ ፭ በሰፈሩት ቁም ነገሮች ላይ ከተነጋገሩ በኋል “እስመ ኀብረ መንፈስ ቅዱስ ምስሌነ ከመ ኢናክብድ ወኢንወስክ ባዕደ ዘእንበለ ዳእሙ ዘንተ(የሐዋ ፲፭፡፳፰)።” ብለው ወሰኑ። ይህም ማለት፤ በነዚህ ርሶች ተብራርተው በቀረቡት ላይ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ተነጋግረን ከወሰነው በቀር ሌላ ባእድና እንግዳ ፈጠራ አልጨመርንም አሉ። ውሳኔ ያስተላለፉባቸው አምስቱ የመነጋገሪያ ቁም ነገሮች የሚለተሉ ናቸው።

፩ኛ፡- “ዝቡሀ ለአማልክት” (ለጣዖት ከተሰዋ)

፪ኛ፡- “ወበደም”        (ደም ማፍሰስና መብላት)

፫ኛ፡- “ወማውታ”       (ያልተባረከ መብላት)

፬ ኛ፡- “ወዝሙት”       (ከዝሙት መራቅ)

፭ኛ፡- “ወዘትጸልኡ ለርእስክሙ ኢትግበሩ ዲበ ቢጽክሙ”

በሀዋርያት ሥራ ምዕራፍ ፲፭ ቁጥር ፳፱ ላይ፤ ከ፩ እስከ ፭ የተዘረዘሩትን እንመልከት።

## ፭ኛ፡-ዝቡሀ ለአማልክት (ለጣዖት ከተሰዋ)

አማልክት ከውጭ ሰርገው የመጡ መንፈስን፤ አካልን፤ አዕምሮን የሚያላሽቁ ከእውነተኛው አምላክ የሚያርቁ ወራሪዎች ባእዶች ናቸው። ለነዚህ ባእዳን ቦታንና ርስትን መልቀቅ፤ ራስን ማስገዛት፤ ግብር መስጠት፤ ገጸ በረከትና መስዋእት ማቅረብ እንደ ባእድ አምልኮ ክልክል ነው።

ዛሬ ወራሪው ወያኔ ራሱ መውረሩ እየገረመን ሳለ። "ዝቡሀ ለአማልክት" ተወላጁን ህዝብ እያፈናቀለ አገሪቷን ምድሪቱን በባእዳን ወራሪዎች እጅ እንድትወድቅ ያደረገበት ዘመን ነው። ተወላጁን ከመሬቱ ከመንደሩ ከሰፈሩ እያፈናቀለ፤ ዜጎችን ለባድ ባለሀብቶች ተገዥ፤ ገባሪና ገጸ በረከት አቅራቢ በሚያደርግበት በዚህ ዘመን፤ በምድረ ኢትዮጵያ አለሁ የሚል ሲኖዶስ ከህዝብ ጎን ቆሞ በግልጽ ካላወገዘ፤ የወገን ፍቅር የጎደለውን ለእውነት ከመጋፈጥ ያፈገፈገውን ይህን መሳይ ሲኖዶስ እንዳለ የሚቆጥር፤ እንቀበለው የሚልስ ዜጋ ምን አይነት ዜጋ ነው?

## ፮ኛ፡-ወበደም (ደም ማፍሰስና መብላት)

"ዘበልአ እምኩሉ ደም አቀውም ገጽየ ላእለ ዛቲ ነፍስ እንተ በልአት ደመ። . . . . . . . . . እስመ ደም ነፍሱ ውእቱ ለኩሉ ዘሥጋ"( ዘሌ ፲፯፡፱_፲፫) የሥጋ ለባሽ ሁሉ ነፍስ ደሙ ነው። "እስመ ነፍስ ተሀድር በደም" ነፍስ በሥጋ የምትቆየው ደም እስካለላት ድረስ ነው። ደም በሌለበት ሥጋ ላይ ነፍስ አትኖርም። የእንስሳ ደም ያለ በቂ ምክንያት ማፍሰስ አፍስሶም መብላት ክልክል ነው። ሊቃውንት አበው ከዚህ በመነሳት የእንስሳት ደም በከንቱ እንዳይፈስ ይጠነቀቃሉ።

ይህም ማለት እንስሳት የተፈጠሩት ለሰባዊ ስልጣን መገለጫዎች ሆነው ነው። ለሰው ክብርና ሥልጣን ተገዥና የክብሩ መግለጫዎች ሆነው ለተፈጠሩት እንስሳት ደም በከንቱ መፍሰስን ይህን ያህል መቃወም የሚጠይቅ ከሆነ፤ የሰውን ደም ማፍሰስ ቀርቶ የወዙን ጠብታ ከንቱ ማድረግ ምን ያህል እጅግ ከባድ የከፋ እንደሆነ መገመት የሚያዳግት አይደለም። የሰራው ቤት በላው ላይ እየፈረሰበት ያለማውን መሬት እየተነጠቀ፤ በሚሰማው ዋይታ ደሙ በሚፈስበት ህዝብ መካከል ያለ ሲኖዶስ; ግፍ የሚሰሩትን "ለእርድ ቀን እንደሚያወፍር ልባችሁን አወፍራችኋል። ጻድቁን ኮንናችኋል ገድላችሁትማል" (ያዕ ፭፡ ፩__፮) በማለት በአንክሮና በአጽንኦ እየተቃወመና እያወገዘ ከህዝብ ጋር የማይቆም ከሆነ ተቀባይነት የለውም።

## ፯ኛ፡-ማውታ (ያልተባረከ መብላት)

በባህላችን እጃችን ያልዳሰሰውን ያልባረክነውን የእንሳትን ሥጋ አንበላም። ምክንያቱ አነጋጋሪና ዘረፈ ሰፊ ብዙ አንድምታ ያለው ነገር ነው። ያልዘራውን ያላጨደውን በፊቱ ያለውን ሁሉ እየዘረፈ የሚበላ ሰው፤ የሞተ እንደመብላት የሚቆጠር እርም መብላት ነው። ሞቶ ከተገኘ የእንስሳ ሥጋ ከመብላት የከፋ ነው። ሌላ ሰው የደከመበትን ወዙ የፈሰበትን መብላት ራስን ከሰባዊ ፍጡረነት ውጭ በማውጣት ደም መጣጭ ቱሀን መሆን ነው። ደሙ በሚመጠጥበት ህዝብና ፤ ቱሀን ሆኖ የሰው ደም በሚመጥ ቡድን መከላከል የሚኖር ሲኖዶስ፤ ተመጣጭንና መጣጭን፤ ከመጣጭነትና ከተመጣጭነት ለማዳን ካልጣረ፤ ክርስቶሳዊና ሐዋርያዊ ሲኖዶስ ተብሎ ሊጠራ አይገባውም።

## ፰ኛ፡-ዝሙት (ከዝሙት መራቅ)

ዝሙትም መጠነ ሰፊ አንድምታ (ሀተታ) አለው። ዝሙት ሲባል በአዕምሯችን ብቅ የሚለውን በተለምዶ አባባል በህግ በቅዱስ ጋብቻ ከተፈቀደው ሩካቤ ውጭ የሚፈጸም ሩካቤ ላይ ብቻ ያተኮረ ይመስላል። ያንድምታው መሠረት ግን "ላንተ ያልተፈቀደልህን ላንተ ለማድረግ አትሞክር" ነው። የህይወት ምንጭ የዓለም መሙያና የመባዣ መሳሪያ አድርጎ በሚራቡ ነገሮች በእጽዋትና በተንቀሳቃሽ ፍጥረታት ሁሉ ያስቀመጠው ሩካቤ ከመስመሩ ሲለቅ በተፈጥሮ ላይ የሚያስከትለው መዛባት ከባድ ነው። ይህ የሚየመለክተው ማነኛውም ከወሰን ያለፈ ሰውረንና ደብቀን የምናደርገው ተግባር ሁሉ ጸያፍ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ወኩሉ ዘእኩይ ምግባሩ ይጸልእ ብርሃነ ከመ ኢይትከሰቶ ምግባሩ" እንዳለው ተደብቀን የምንሰራው ሁሉ የተወገዘና የተጠላ ክፉ ዝሙት ነው።

ከገዳም ወጥተው ከህዝብ ጋራ ተቀላቅለው በመኖር በዝሙት ህብረተ ሰብን በመበከል ላይ ያሉትን አስመሳይ መነኮሳት ከህዝቡ ለመለየት የማይጥር ሲኖዶ፤ የራሳቸውን ትዳር አፍርሰው የሰው ትዳር በማፍረሳቸው ህዝቡ የሚማረርባቸውን አስመሳዮች ቄሶችን ቀድሰው ከማቁረብ እንዲወገዱ፤ የራሳቸውን ስም ከራሳቸው ሰርቀውና ደብቀው እየጻፉ በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን የሚበትኑትን የጨለማ ቡድን (ሠራዊተ ጽልመት) አስመሳይ ካህናትን ከማውገዝ ይልቅ እንዲያውም በዝሙቱ እንዲቀጥሉ የሚተባበሩ ጳጳሳት የሚሳተፉበት ሲኖዶስ ተቀባይነት የለውም።

## ፳ኛ፡-“ዘትጸልኡ ለርእስክሙ ኢትግበሩ ዲበ ቢጽክሙ”

“ዘትጸልኡ ለርእስክሙ ኢትግበሩ ዲበ ቢጽክሙ” “በራሳችሁ ሊደረግባችሁ የምትጠሉትን በሌላ ሰው ላይ አታድርጉ” በሰው መካከል ችግር የሚፈጠረው በራስ ላይ ሊደርግ የማይፈለግ ሁሉ በሌላው ላይ ለማድረግ ሲሞከር ነው። ይህ ትእዛዝ የማይገሰስ በቦታ በጊዜ የማይሻሻል መለኮታዊ ዶክትሪን ነው። ቅዱስ ሲኖዶስ ብሎ ራሱን የሚጠራ ስብስብ ይቅርና፤ የቤት አባ ወራወችና፤ የቤት እመቤቶች ለልጆቻቸው፤ የመንደር ሽማግሌዎች ላካባቢያቸው ሊናገሩት ሊመክሩት የሚገባ ትእዛዝ ነው።

ሐዋርያት በውሳኔያቸው ያካተቷት “በራሳችሁ ሊደረግባችሁ የምትጠሉትን በሌላ ሰው ላይ አታድርጉ” የምትለው ይህች አረፍተ ነገር፤ ለሰው ልጅ ክብርና የነጻነት መሠረት ናት። ከዚህች አረፍተ ነገር በኋላ የተናገሩት “እስመ ሀብረ መንፈስቅዱስ ምስሌነ ከመ ኢናክብድ ወኢንወስክ ባእደ ዘእንበለ ዳእሙ ዘንተ” (ቁ ፳፰) የሚል ከባድ ንግግር ነው። ማለትም የማይጠቅም ሸክም በህዝብ ላይ እንዳንጭንበት መንፈስ ቅዱስ መንፈሳችንን በመቃኘት ተባበረን።” ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት የህዝቡን ሁለንተና መዳሰስ ከሚያስችሉ ከ፩ እስከ ፳ ተራ ቁጥር ላይ ሌላ ባእድ ነገር ላለመጨር በመጠንቀቅ ወሰኑ። ይህንንም ውሳኔ “ወለእመ አቀብክሙ ነፍስክሙ እምእሉ ምግባራት ትሄልው በሰላም”(የሐዋ ፲፭፡፳፯—፳፱) ማለት ከእነዚህ ነገሮች ራሳችሁን ከጠበቃችሁ ኑሯችሁ ሁሉ ሰላም የሰፈነበት ይሆናል።” ብለው ዘጉ።

የዚህች ቤተ ክርስቲያን ቄስ ነኝ የምትል ከሆነ ከመንፈሳዊ ሀላፊነት አትሸሽ! የወያኔ ፓትርያርክ አባ ማትያስ፤ ኢሀደግ በኢትዮጵያ የዘረጋውን የጥፋት መረብ ደብቀው፤ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት በጥርጥር የሚመለከቱትን በዓለም ትዝብታ ላይ የወደቀውን የወያኔውን ልማት “ዓለም ያደነቀው” በማለት፤ የዘንድሮውን ርክበ ካህናት የከፈቱበትን ከመስመር የወጣውን ንግግር በጥሞና አዳምጥ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በዘረጉት ያብነት ጉባዔ ተሳትፌያለሁ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ትክክለኛ ቄስ ነኝ የምትል ከሆነ፤ ያስጎበኘሁህን አይተህ፤ የነገርኩህን ሰምተህና ተረድተህ፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መምህራን ካስተማሩህ የልማት ዘይቤ ጋራ አነጻጽረህ በክህነታዊ ሀለፊነትህ የምትለው ለማለት አትፍራ”

ለዘንድሮው ርክበ ካህናት አቡነ ማትያስ ያቀረቡትን የመክፈቻ ንግግር በሰጠሁህ ቅርጽና ይዘት ለክተህ፤ እያስተማሩ ባሳደጉህ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ልማታዊ መስፈርት ሰፍረህ “ልማታዊ ፓትርያርክ” በሚል ርእስ አቅርብ፤ ብለው ዶ/ር ደስታው አንዳርጌ ያዘዙኝ የመሰለኝን ለመፈጸም መስፈርቱን ከዚህ በላይ አስቀምጫለሁ።

በተረፈ፤ በመላ ኢትዮጵና በዓለም ዙሪያ ያለው ህዝባችን አሁን ባለበት እጅግ በከፋ ሁኔታ ላይ ሳለ፤ በነ አቶ ስብሀት ነጋ እየተገፉ በመንበረ ፓትርያርካችን ላይ የተቀመጡት በመላ ኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ምንም ክፉ ነገር እንደሌ ለማስመሰል “ካዲስ አበባ ወጥቼ በየገጠሩ ስዘዋወር ዓለም ያደነቀው ልማት ሲጣደፍ አየሁ” ባሉት በአቡነ ማትያስና፤ በሳቸው አማካይነትም ወያኔ በሚቃኘው ሲኖዶ ቤተ ክርስቲያናችንን እንዳይለካት ይረዳው ዘንድ፤ ያቡነ ማትያስን ፓትርያርካዊ የመክፈቻ ንግግር ከራሴ ማብራሪያ ጋራ ለመላ ኢትዮጵያውያን ከዚህ ቀጥየ በማቀርባት ክታብ እስክንገናኝ እግዚአብሄር በያለንበት ይጠብቀን።

ይቆየን።

ለሌሎች ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ ጦማሮች የሚከተለዉን ድህረ-ገጽ ይመልከቱ።

http://www.medhanialemeotcks.org/